በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

የፕሬስ መግለጫ PRESS RELEASE

# በአፍሪካ ቀን ዝግጅት ኢትዮጵያ ደማቅ ተሳትፎ አደረገች

በደቡብ ኮርያ ሴዑል ከተማ በቅርቡ በተከበረው 49ኛው የአፍሪካ ቀን ዝግጅት ላይ ኢትዮጵያ ደማቅ ተሳትፎ አደረገች፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ጽ/ቤት እንዳስታወቀው ኢትዮጵያን ጨምሮ በደቡብ ኮሪያ የአፍሪካ አምባሳደሮች ቡድን ባዘጋጀው በዚሁ ዝግጅት ላይ የደቡብ ኮሪያ የውጭ ጉዳይ ም/ሚኒስትር ባደረጉት ንግግር በኮሪያና አፍሪካ የተመሠረተው ጠንካራ ትብብር በአፍሪካ–ደቡብ ኮሪያ የትብብር ፎረም ይበልጥ እየተጠናከረ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በቅርቡ ተከፍቶ ሥራውን የጀመረው የኢትዮጵያ ኤምባሲም በደቡብ ኮሪያ በትምህርት ላይ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ በመሆን በዝግጅቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ አድርጓል፡፡ በዝግጅቱ የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች ጨዋታ፣ ባህላዊ ምግቦችና የቡና አፈላል ሥነ–ሥርዓት የቀረበ ሲሆን የኢትዮጵያ የንግድ፣ ኢንቨስትመንትና የቱሪዝም መስህቦች በዝግጅቱ ላይ የታዳሚዎችን አድንቆት አግኝቷል፡፡ ይህ ዝግጅት ከተከፈተ አጭር ጊዜ ካስቆጠረው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በደቡብ ኮሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከቅድመ ዝግጅቱ አንስቶ በወቅቱ አገራቸውን በበጎ መልኩ በማስተዋወቅ ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረጉበትን አጋጣሚ ፈጥሮ አልፏል፡፡

ቃል አቀባይ ጽ/ቤት
ሰኔ 01 ቀን 2004 ዓ.ም.